# 4.የሚያስፈልግዎን ዋና ነገር ማሟላት የሚችሉት እንዴት ነዉ?

## በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የሚከተሉትን ይማራሉ፡፡

- የሚያስፈልግዎ ዐብይ ነገር ምንድን ነዉ?
- ይህን የሚያስፈልግዎ ዐብይ ነገር ኢየሱስ እንዴት የሚያሟላዉ እንዴት ነዉ?
- ኢየሱስ አዳኝዎ ነውን?
- ሌሎች ፍላጎቶችዎስ?

## ክፍል 1

### የሚያስፈልግዎ ዋና ነገር ምንድን ነው?

*ለአካልዎ ወይስ ለነፍስዎ?*

በምድረ በዳ ወይም በጫካ ውስጥ የጠፋ ሰው ወይም በታንኳ የሚሄድ ሰው አቅጣጫውን ቢስት ተፈልጎ መዳን አለበት፡፡ የተራበ ሰው ምግብ ያስፈልገዋል፣ የተፈረደበት ዕስረኛ ምህረት ያስፈልገዋል፡፡ በመርዝ የተጎዳ ሰው መፍትሔ ያስፈልገዋል፡፡

እነዚህ ሁሉ ነገሮች በጣም አስፈላጊዎች ቢሆኑም ሌላ የሚያስፈልግዎ የበለጠ ነገር አለ፡፡ ከአካል ያለፈ ነገር አለዎ፡፡ እርሱም መንፈሳዊ ተፈጥሮ ያለዉ ነፍስዎ ነዉ፡፡ ነፍስዎ በውስጥዎ ያለው የህልዉና ምንጭ ይሁን እንጂ ያለ እዚአብሔር ከሆነ ግን የተበላሸ ነው፡፡ ልክ በውሃ ጥም እንደሚሞት ሰው ይሆናሉ፡፡ ለአካልዎ ከሚያስስፈልጉ አጣዳፊ ነገሮች ይልቅ ለነፍስዎ የሚያስረፈልጉ ሕይወት እና ጤንነት የሚበልጡ ነገሮች ናቸዉ፡፡

**ሮሜ 5:12** «ስለዚህ ኃጢአት በአንድ ሰው በኩል ወደ ዓለም እንደገባ ሁሉ ሞትም በኃጢአት በኩል ገብቷል፣ በዚሁ መንገድ ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ መጣ፤ ምክንያቱም ሁሉም ኃጢአት ሰርተዋል»

## የሚያስፈልግዎ ትልቁ ነገር አዳኝ ነዉ

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን የሰው ነፍስ የጠፋ፣ እየተራበ ያለ፣ ለሞት በማያደርስ ህመም የታመመ፣ እና ሞት የተፈረደበት ነው። ሰው ፈልጎ የሚያገኘዉ፣ የሚመግበዉ፣ የሚፈውሰው እና ኃጢአቱን ይቅር የሚልለት አዳኝ ያስፈልገዋል። ትልቁ የሚያስፈልግዎ ነገር አዳኝ የሆነበት ምክንያት ራስዎን ማዳን ስለማይችሉ ነው።

- ክርስቲያን ወላጆች ስላሉዎ አይድኑም
- የቤተክርስቲያን አባል መሆን አያድንም
- ጥሩ ሰው ለመሆን መሞከር አያድንዎም
- ያለአዳኝ መዳን አይችሉም

<table>
<tr><td>

**የሚከተሉትን ይስሩ**

ሰው ሊኖረው የሚችለውን ትልቅ ችግር የሚገልጸው የትኛው ሐረግ ነው ከስሩ ያስምሩበት
የአካል በሽታ፣ መንፈሳዊ ሞት፣ የምግብ ዕጥረት

እኔ /የራስዎ ስም/ ብዙ የሚያስፈልጉኝ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከሁሉም የሚበልጠው የሚያስፈልገኝ ነገር ...____________ነው፡ ምክንያቱም ራሴን ከኃጢአትና ከሞት._._.______ አልችልም።<br>
ኢየሱስ ክርስቶስን ከዚህ በፊት እንደግል አዳኝዎ አድርገዉ የተቀበሉ ቢሆንም ይህ ክፍለ ትምህርት አሁንም የሚጠቅምዎ ነገር ነው። እንዴት በየዕለቱ እንደሚያረዳዎ ይነግርዎታል።

</td></tr>
</table>

# ክፍል 2

## ኢየሱስ የሚያስፈልግዎን ዋና ነገር የሚያሟላልዎ እንዴት ነዉ?

### እግዚአብሔር የላከልዎ አዳኝ ኢየሱስ ነው

ጠፍቶ የነበረውን እና እየተራበ ያለውን ነፍስዎን ፈልጎ ይመግብ እና ከበሽታ ይፈው ዘንድ እግዚአብሔር ልጁን ላከ። በእኛ ምትክ በመሞት የኃጢአት ይቅርታን ይሰጥዎ ዘንድ ሰው ሆነ። ስሙ ኢየሱስ ነው፤ ትርጉሙም አዳኝ ማለት ነው። እርሱ ብቻ ነው ሊያድንዎ የሚችለው።

## ይህን ጥቅስ በቃልዎ ያጥኑ

**ሐዋ 4፡12** «ድነት በሌላ በማንም አይገኝም እንድንበት ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ከዚህ ስም በስተቀር ሌላ ስም ከሰማይ በታች የለምና፡፡»

## ኢየሱስ እውነቱን እና መንገዱን ያሳይዎታል

ሰይጣን አዕምሮአችን በስህተት እና በአለማመን አሳውሮታል፡፡ ከእግዚአብሔር ርቀን መንገዱ ጠፍቶብናል ዲያቢሎስ የእግዚአብሔርን ቃል፣ ኃይል፣ ጥበብ፣ መልካምነትና ፍቅር እንድንጠራጠር ሊያደርገን ይሞክራል፡፡ አንዳንድ ሰዎች ከነጭራሹ እግዚአብሔር መኖሩን ይጠራጠራሉ፡፡

**2ቆሮ 4፡4** «የእግዚአብሔር አምሳል የሆነውን የክርስቶስ፣ የክብሩን ወንጌል ብርሃን እንዳያዩ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን ሰዎች ልቦና አሳውሮአል፡፡»

ሰይጣን ብዙ ሰዎችን በሐሰተኛ ሐይማኖቶች ያታልላል፡፡ አንዳንዶች ወደ መናፍስት ወይም ምስሎች ይጸልያሉ፡፡

**ሮሜ 1፡23** «የዘላለም አምላክን ክብር ምውት በሆነው ሰው፣ በወፎች፣ በእንስሳትና በምድር ላይ በሚሳቡ ፍጥረት መልክ መስለው ለወጡ፡፡»

ሰይጣን ለእኛ መልካም ስለሆነዉ እና ክፉ ስለሆነዉ ነገር ይዋሽናል፡፡ ደስታን ፍለጋ በስህተት መንገድ በመግባት ከሕይዎት መንገድ ርቀን እንገኛለን፡፡

ከሰይጣን በተቃራኒ መልኩ ደግሞ ኢየሱስ ሊፈልገን፣ እና ወደ ደስታ፣ እና የዘላለም ህይወት ለማስገባት ወደ እግዚአብሔር ይመራናል፡፡ በእርሱ እና በትምህርቱ እውቀትን በማወቅ ከአለማመን እና ከስህተት ነጻ መሆን ይችላሉ፡፡

## እነዚህን ጥቅሶች በቃልዎ ይያዙ

**ዮሐንስ 14፡6** «ኢየሱስም እንዲህ አለው መንገድ እኔ ነኝ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም፡፡»

**ሉቃ 19፡10** «ምክንያቱም የሰው ልጅ የመጣው የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን ነው፡፡»

**ዮሐ 8፡12** «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝም የህይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ ከቶ በጨለማ አይመላለስም፡፡»

**ዮሐ 8:32** «እውነትንም ታቃላችሁ እውነትም ነጻ ያወጣችኋል:: »

ማንም ሰው በቅንነት ወደ እግዚአብሔር ከመጣ እና እውነትን አውቆ ሊኖርበት ከፈለገ እግዚአብሔር ያሳየዋል:: መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ክፍት በሆነ አእምሮ ይጸልዩ እግዚአብሔር የሚፈልገውንም ለማድረግ ፈቃደኛ ይሁኑ::

**ዮሐ 7:17** «ማንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ቢፈልግ የእኔ ትምህርት ከእግዚአብሔር ወይም ከራሴ የመጣ መሆኑን ለይቶ ያውቃል::»
**ኤፌ 4:23-24** «ደግሞም በአእምሮአችሁ መንፈስ እንድትታተደሱ እውነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረውን ኢየሱስን እንድትለብሱ ነው::»

**የሚከተሉትን ይስሩ**

ኢየሱስ ወይም ሰይጣን በማለት መልስ ይስጡ::

- መልካም ስለሆነው ነገር የሚያሳውረን ማን ነው?
- እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል የሚያሳየን ማን ነው?
- ከስህተት እና ከአለማመን ነጻ የሚያደርገን ማን ነው?
- የእግዚአብሔርን ቃል እንድንጠራጠር የሚያደርገን ማን ነው?
- ሰዎችን ወደ ሐሰተኛ ሐይማኖት የሚመራ ማን ነው?

# ፀሎት

***እግዚአብሔር ሆይ እውነትን ያስተምረኝ ዘንድ ልጅህን ኢየሱስን ስለላከው አመሰግንሃለሁ:: እባክህ እውነቱን አሳየኝ፤ የሚከፈለውንም ዋጋ ሁሉ ከፍዬ እንድኖርበት እርዳኝ::***

## ገዳይ የሆነ የልብዎን ኃጢአት ኢየሱስ ያስወግዳል።

ሐጢአት ማለት የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መተላለፍ መሆኑን ተምረዋል። ስለዚህ ከሁሉ የሚብሰው ሐጢአት የእግዚአብሔርን ዋነኛ እና አስፈላጊ ትዕዛዝ መተላለፍ ነው ማለት ይቻላል። ይህ ትልቁ ትዕዛዝ ምን እንደሆነ ኢየሱስ ነግሮናል።

**ማቴ 22፡37-39** «እርሱም እንዲህ አለው፣ ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህ ውደድ፣ ይህ የመጀመሪያውና ከሁሉ የሚበልጠው ትእዛዝ ነው። ሁለተኛውም ያንኑ ይመስላል፣ ይህም ጎረቤትህን እንደራስህ ውደድ። የሚለው ነው።»

ሁላችንም ሁለቱን የእግዚአብሔርን ዋና ዋና ትዕዛዛት ጥሰናል። የሐጢአት ሁሉ ስር የሆነው ራስ ወዳድነት ልባችንን ሞልቶ ፍቅራችንን አደብዝዟል። ለእግዚአብሔር ፍቅር የሰጠነው ምላሽ ምስጋና ቢስነት እና ከእርሱ ጋር አለመስማማት ነው። ለእግዚአብሔር ወይም ለሌሎች ከምናስበው በላይ ለራሳችን እናስባለን። በራስ ወዳድነት ላይ ያተኮረው ልባችን በግለሰቦች እና በህዝቦች መካከል ኃጢአተኛን ዓለም ያፈራል።

**2ጢሞ 3፡2-4** «ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉ፣ ገንዘብን የሚወዱ፣ ትምክህተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ ፍቅር የሌላቸው፣ ለዕርቅ የማይሸነፉ፣ ሐሜተኞች፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ ጨካኞች፣ መልካም የሆነውን የማይወዱ፣ ከዳተኞች  ችኩሎች፣ በከንቱ በትዕቢት የተወጠሩ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉና።»

## ኢየሱስ ከኃጢአት ሊያነጻዎ እና በእግዚአብሔር ፍቅር ሊሞላዎ መጣ።

**1ዮሐ 1፡9፣7** «ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከአመጻም ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው። ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ፣ እኛም በብርሃን ብንመላለስ እርስ በእርሳችን ህብረት አለን፣ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።»

**ሮሜ 5፡5** «እግዚአብሔር በሰጠን በመንፈስ ቅዱስ ፍቅሩን በልባችን አፍስሶአልና።»

**የሚከተሉትን ይስሩ**

ሁለቱን የእግዚአብሔር ታላላቅ ትዕዛዞች ጥሰዋልን?

**2ጢሞ 3:2-4**ን እንደገና ያንብቡና በውስጡ ከተጠቀሱት ኃጢአቶች መካከል በህይወትዎ ቢያንስ አንድ ጊዜ የተላለፉባቸውን ኃጢአቶች ያስምሩባቸው።

እግዚአብሔር ይቅር እንዲልዎ እና በፍቅሩ እንዲሞላዎ ይጠይቁት።

## ኢየሱስ የኃጢአትን እና የሰይጣንን ኃይል ይሰብራል።

የሚገባንን ነገር ማድረግ እስከማንችል ድረስ ኃጢአት የዉሳኔ አቅማችንን አዳክሞታል።

**ዮሐ 8:34** «ኃጢአትን የሚያደርግ የኃጢአት ባሪያ ነው»

**ሮሜ 7:14፣15፣18** «እኔ ግን ለኃጢአት እንደ ባሪያ የተሸጥሁ ስጋዊ ነኝ ለማድረግ የምፈልገውን አላደርግም ነገር ግን የምጠላውን ያን አደርጋለሁና በጎ የሆነውን የማድረግ ምኞት አለኝ ነገር ግን ልፈጽመው አልችልም።»

ኢየሱስ ከኃጢአት እስራት ነጻ አውጥቶ ከመጥፎ ሱሶች ሁሉ ይፈታል። ከቁጥጥር ውጭ ከሆነ ቁጣ፣ ከዝሙት፣ ከማታለል፣ ከስርቆት፣ እና ከውሸት ነጻ ያወጣናል፣ ጎጂ ከሆኑ ሱሶች ማለትም ከአልኮል መጠጥ ሱሰኝነት፣ ከሲጋራ፣ ከአደንዛዥ እጸችና እና ከቁማር ነጻ ያወጣል። የርኩሳን መናፍስትን እና የሰይጣንን ኃይል ይሰብራል።

### የሚከተለውን ጥቅስ በቃልዎ ይያዙ

**ዮሐንስ 8:36** «እንግዲህ ወልድ ነጻ ካወጣችሁ፣ በእውነት ነጻ ትወጣላችሁ።»

## ኢየሱስ በእርስዎ ቦታ በመሆን ምህረትን አስገኝቶልዎታል

እግዚአብሔር ቅን ፈራጅ ስለሆነ ኃጢአትን አያልፍም። ሞት እግዚአብሔር ኃጢአትን የሚቀጣበት እና የኃጢአት ውጤት ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር እጅግ ስለወደደዎ በእርስዎ ቦታ ይሞት ዘንድ አንድ ልጁን ላከው። ኢየሱስ የሞተዉ ለእርስዎ ሞትክ ሆኖ ነበር። እንደገና በመነሳቱና ወደሰማይ በማረጉ እርስዎም ያንኑ መሆን ይችላሉ።

**1ጴጥ 2፡24** «ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት መስቀል ላይ ተሸከመ»

**ገላ 2፡19፡20** «ለእግዚአብሔር እኖር ዘንድ፣ በሕግ በኩል ለሕግ ሞቻለሁና። ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፣ ከእንግዲህ እኔ አልኖርም፤ ነገር ግን ክርስቶስ በውስጤ ይኖራል። አሁንም በሥጋ በምኖረው ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን አሳልፎ በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለኝ እምነት ነው።»

ኢየሱስን እንደ አዳኝዎ አድርገዉ ሲቀበሉ የዕርሱ ሞት ሞትዎ እንደሆነ ህይቱም ህይወትዎ እንደሆነ መቀበልዎ ነው። በዚያ ደቂቃ ውስጥ የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናሉ። ኃጢአት ከእግዚአብሔር ለይቶዎ ነበር፣ ነገር ግን በኢየሱስ በኩል ይቅርታን፣ አዲስ ሕይወትን፣ እና ከእግዚአብሔር ጋር ህብረትን ያገኛሉ።

**የሚከተሉትን ይስሩ**

በሐጢአቴ መሞት የለብኝም ምክንያቱም ኢየሱስ

..................................................................................................................

..................................................................................................................

ኢየሱስ ነጻ እንዲያወጣዎ የሚፈልጉት ልማድ ካለብዎ ነፃ እንዲያወጣዎ በጸሎት ይጠይቁት

# ክፍል 3

## ኢየሱስ አዳኝዎ ነውን?

**ውሳኔው የግልዎ ነው**

ኢየሱስ አዳኝዎ ለመሆን ፈቃደኛ ነው፣ ነገር ግን እንዲቀበሉት አያስገድድም።

**እርሱን ለመቀበል ጊዜው አሁን ነው።**

በኋላ የማይቻልበት እና የተዘጋ ጊዜ ሊሆን ይችላል። ከዚያም አልፎ ይህን አዲስ ሕይወት በየቀኑ እየኖሩ መደሰት እንዲችሉ ዛሬ እርሱ የልብዎን በር ያንኳኳል። ወደ ውስጥዎ ይጋብዙት።

***ራዕ 3:20*** *«እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ዕብራዊያን **3:15** «ዛሬ ድምጹን ብትሰሙ ልባችሁን እልከኛ አታደንድኑ።»*

***2ቆሮ 6:2*** *«እነሆ ትክክለኛው ሰዓት አሁን ነው፣ የመዳንም ቀን አሁን ነው»*

**የሚከተለውን ይስሩ**

ኢየሱስ በአጠገብዎ ስላለ ጸሎትዎን መስማት ይችላል

በራስዎ አገላለጽ ለኃጢአትዎ ስለሞተልዎ አመስግነው አዳኝዎ እንዲሆን ይጠይቁት። ይህን ዉሳኔ ከዚህ በፊት አድርገዉ ከሆነ የሚያስፈልግዎን ሌሎች ነገሮች ስለሚያሟላልዎ በእምነት ያመስግኑት።

# ክፍል 4

## ሌሎች ፍላጎቶችዎስ?

**የሰማዩ አባትዎ ያስብልዎታል**

**ማቴ 31:33** «ስለዚህ ምን እንበላለን ምን እንጠጣለን ምንስ እንለብሳለን ብላችሁ አትጨነቁ፣ አሕዛብ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለማግኘት ይጨነቃሉና የሰማዩ አባታችሁ እነዚህን ሁሉ ለእናንተ እንደሚያስፈልጋችሁ ያውቃል። ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግስትና ጽደቁን እሹ፣ እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል»

## ስለሚፈልጉት ነገር በየቀኑ ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገሩ

**ፊሊ 4:6** «በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ፣ ከምስጋናም ጋር ልመናችሁን በእግዚአብሔር ፊት አቅርቡ እንጂ ስለማንኛውም ነገር አትጨነቁ።»

## ኢየሱስ ፈዋሽዎ ይሆናል

በሚፀለይበት ጊዜ መልስ በመስጠት ኢየሱስ የታመሙትን ይፈውሳል።

**ሐዋ 10:38** «ኢየሱስ በደረሰበት ሁሉ መልካም እያደረገ በዲያቢሎስ ስልጣን ስር የነበሩትን ሁሉ ፈወሰ»።

**ዕብ 13:8** «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት ዛሬም ለዘላለምም ያው ነው።»

**ይህን ይስሩ**

ስለሚያስብልዎ ያመስግኑና ስላለብዎ ማንኛውም ችግር እንዲረዳዎ በጸሎት ይጠይቁት።

## ክፍለ ትምህርት አራትን ስላጠናቀቁ እንኳን ደስ አለዎ።

*አሁን የክፍለ ትምህርት አራትን ጥያቄዎች በዚህ ትምህርት መጨረሻ ገጽ ላይ ከሚገኙት የክፍለ ትምህርት መከለሻ ጥያቄዎች መካከል መልሳቸውን ከሰጡ በኋላ ክፍለ ትምህርት አምስትን ያጥኑ። ስድስቱት ትምህርቶች ካጠናነቀቁ እና ለችያቄዎች መልሶችዎን ከላኩልን በኋላ ሰርቲፊኬት እንልክልዎታለን*

# *እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርክዎ!*